# መለስ ሳይመሽ፤ተመሸ! EthioLion የጐንቻው!

ንጉሡን ዙፋን ስር ቁም የቀበረው፤
ስድሳ ሹም ሚኒስትር ቀን-ነፍስ የበላው፤
ቀዳማዊያን ፈጅቶ ሺህ ያልጠቀመው፤
ሞትን የሚገድል አራጅ የሚያርደው፤
ስለቱ አድባር ቆሌ መጋዝ ሰው-በሰው፤
ተጣርሶ ተናክሶ በአጥንት የዶመው፤
ዛቢያው ምሳር ሰብሮ 'ባለእጅ'፤የሠራው፤
ሽፍቶችን ከዋሻ ፤ እልፍኝ፤የናኘው፤
ይገለባበጣል ጊዜና ቦታው፤
ቅል ድንጋይ ይሰብራል በለስ ሲቀናው፤
**መለስ ሳይመሽ ተመሸ! ጓዳህ አፋፍ ነው።**

ስንት የጦር መኳንንት ትጥቅ ያስፈታው፤
ትኩስ ደም-አበላ በእርሳስ የቀዳው፤
'ተረጋግጠው ምሁር' ባለ እራስ አልቦው፤
ማማው ቤተ-መንግሥት መሰቃቀያው፤
ሲወርዱ በሽምቀቅ አንገት ማስገቢያው፤
የአጼዎቹ ምግባር የዓለም ዘውድ መድፊያው፤
ዋንጫዎ ተሞልቷል እድር መጠጫው፤
ፈርሷል ሰገነቱ፤ ምርጫ ማምለጫው፤
**'መለስ' መንግሥትዎ ወለድ መክፈያው።**

ኮሎኔል መንግሥቱን ከድቶ ያስከዳው፤
አዋርዶ አወራርዶ ስደት የጣለው፤
ሲመክሩት ባይሰማ በትብዒቱ ነው፤
ሙታንን በሰማይ አሕዛብን በምድር የሚያናውጠው፤
ሹም ሽሩ ይብላላል መሃል ዙር ገባው፤
ማዕበሉ አልሰከነም ከርሰ-ምድር ነው፤
ሕዝብ አገር በጅምላ በሽብር አስረው፤
በአናትዎ ዙሯል፤የበደል ቁናው፤
**መለስ ሳይመሽ ተመሸ! ሳይጨንቅህ መውጫው።**

በቃሉ 'አፈላማ' ነፍስ የገበረው፤
ጣዕረ-ሞት ዳርገውት አፈር የቃመው፤
ሰብ አካሉ ፈርሶ ድምጹ ኃያው ነው፤
ደሙ ኅይዎት ዘርቷል የአምና ታቻምናው፤
በልጉ ሲያጉረምርም ከሰማይ ኃዋው፤
በምድር፤ ያስተጋባል በደጅ በጓሮው፤
አጥንቱ ስር ሰዷል በደም የራሰው፤
በጥቅምት በኅዳር በቀል ማጨጃው፤
መኸር ከደርሱ ከአግማስ አውድማው ፤
የሕይዎት እስትንፋስ ቃል-ድምጽ ተናዘው፤
ትውልድ መመማሪያ ድንጋይ ታቅፈው፤
'ቤን አሊን፤ሙባረክ፤ጋዳፊን'፤ሆነው፤
ወይ ምህረት ወይ ሽረት'መስቀል ተባርከው'፤
እርስዎን-ውርስዎን 'ዓለም ጣጥለው'፤
ዘር ካደቆኑበት፤ 'ቆረጥ-ደብተራው'፤
'ስርጥ''እንዲያቀስሱ'፤ደደቢት፤ዋሻው፤
**'ዘላለም እንዲያርፉ' ምድር ጥግ ይዘው።**

yegonchaw@yahoo.co.uk የጐንቻው!
Ethiopia Will Prevail!

EthioLion.Com